# ለመኢአድ ሐቀኛ አባላት
# ጽኑ ድጋፍ ላላችሁ ሁሉ!
# አጣዳፊ ብሔራዊ ጥሪ

*(ከደጋፊዎች)*

እናት አገራችን በዘረኞች ተረግጦ በጠመንጃ አፈሙዝ ተሰቅዛ በባንዳ አጋሚዶ ከተያዘችበት ከመነሻ አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት የኢትዮጵያን አንድነት ዋና መሰረታዊ መርሆ ያዳረገ ለልዕላዊነቷ፣ ለሕዝቧ አንድነት፣ ለታሪክ ክብርና ኩራት፣ ለሕግ የበላይነት የቆመና የታገለ ከፍተኛ መስዋዕትነትን ለረዥም ዓመታት የከፈለ ትልቅ ብሔራዊ ድርጅት ነው።

ወያኔ የፈጠረውን የቋንቋ ልዩነት መከፋፈልና እርስበርስ ጥላቻና ብጥብጥን መኢአድ ተቃውሞና ተቋቁሞ በኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ላይ በፅናት ተመስርቶ ኅብረታችንን፣ አንድነታችንን ኢትዮጵያነታችንን በመስበክ ሁሉንም ብሔር-ብሔረሰብ ወደ አንድ ኢትዮጵያ ቀዳሚ ዜግነት መንፈስ ያሰባሰበ ድርጅት ነው።

በዚህም የሕዝብ ብቸኛ ተስፋና ያገር ኩራት ሆኖ በኢትዮጵያ ሕዝብ የታቀፈና አመኔታን ያተረፈ ድርጅት ሆኖ ቆይቷል።

የመኢአድ የትግል ሂደት እጅግ ፈታኝና ብዙ ውጣ ወረድን፣ የብዙ አባላትን መስዋዕትነት የጠየቀ እና የኢትዮጵያ ሕዝብን በቆራጥነት በፅናት ለአገሩ ለአንድነቱና ለመብቱ እንዲታገል የስልጣን ባለቤትነትና የሕግ የበላይነትን ለማስጨበጥና ለማረጋገጥ በቀደምትነት የመራ ድርጅት ነው፡

ከእንግዲህ ወዲህም ያለውን ጊዜ ከምንጊዜውም የበለጠ በመኢአድ ማዕከላዊ አመራር የመላ ኢትዮጵያን ሕዝብ የነቃ ተሳትፎና የሞት ሽረት ትግል የሚጠይቅ እጅግ ፈታኝና እጅግ ወሳኝ ጊዜና ሂደት ነው።

እውነት ለእናት አገራችን፣ ኢትዮጵያ በረሃብና በበሽታ እየረገፉና በመብት በዜግነት እጦት ተረጋግጠው ክፉኛ እየተሰቃዩ ለሚገኙት፣ ለሚሰደዱት ሕዝባችን ከልባችን የምንቆረቆር ከሆነ፣ ይኸን ከፊታችን የተደቀነውን ወሳኝ የትግል ወቅትና የፈተና ጊዜ በውል ለመረዳትና ለመቋቋምም ምን ማድረግና ምን ወሳኝ ለውጥ ማምጣት እንዳለብን መገንዘብና ለተግባራዊነቱ በቁርጥ መዘጋጀትና መሰለፍ አለብን።

በወያኔ ፓርቲ የውስጥ አመለካከት መሰረት <u>መኢአድ</u> በድርጅታዊ ጉልበቱ በተለይም <u>ደግሞ</u> በአመራር ብቃቱ ላይ የዓይነት ለውጥ አድርጐ ከተንቀሳቀሰ እንደሚያሸንፍና መንግሥት እንደሚሆን የታመነበት ሲሆን፤ ይህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ የሆነ አንጋፋ ድርጅት እዚህ ብሔራዊ ድል ላይ እንዳይደርስ የተጠነሰሰለት ሴራና የተደገሰለት ውድቀት ደግሞ ቀላል እንዳልሆነ ከዚያው ከወያኔ አካባቢ በተገኘው የውስጥ መረጃ ተረጋግጧል።

ይህ በዚህ እንዳለ፣ የሚያሳዝነው የመኢአድ መሪዎች ይህን የወያኔ የፖለቲካ ሴራና አድማ የአፋኝ ሥርዓት እያወቁ ለራሳቸው የሥልጣን ጥማት፣ የጥቅም እሽቅድድም፣ የስለላና የፖለቲካ ቅሌት ተገዥ ሆነው ድርጅቱን ለጠላት አጋልጠው እያኰላሹና እያሰናከሉ ይገኛሉ። በመካከላቸውም ክፍፍል፣ ለወያኔ የመሰለልና የማጐብደድ ክህደት፣ ሻጥርና ተንኰል በዝቶ ማዕከላዊነትና ድርጅታዊ ዲስፕሊን ጠብቆ መስራት ተስኖአቸው ድርጅቱ ከፖለቲካ ፈሩ ለቆ፣ የአባላት አንድነት ጠፍቶ ድርጅቱን ወደ መበትንና መፍረሱ አድርሰውታል።

ስለሆነም በአሁኑ ወቅት ትኩረት ሆኖ አጣዳፊ መፍትሔ እየጠየቀ ያለው ጉዳይ የመኢአድ አመራር አባላት ሁኔታ ነው።

ከላይ የተመለከተውን ጸረ- መኢአድ የወያኔ ሴራና አድማ ለመቋቋምና መኢአድን ለአስተማማኝ ድል ለማብቃትና ሕዝብን የሥልጣን ባለቤት ለማድረግ ያለው ምርጫ አንድ ነው።

ይኸውም አሁን ያለውን ደካማና ቅሌታማ አመራር እንደ ጠላ ቂጣ እያገላበጡ ከመምረጥ ይልቅ እነሱን በሙሉ አንስቶ የድርጅቱ ሙሉ አባላት ንቁና ሐቀኛ ተሳትፎ በሚንፀባረቅበት ጠቅላላ ጉባኤ የፖለቲካ፣ የድርጅት አመራር ብቃትና፣ ፅናት፣ እውቀት፣ ጥበብና አስተዋይነት ያላቸው ቆራጥ ያልተነካኩ፣ የሥልጣን ጥማት አልባ፣ የአገርና ሕዝብ ወዳድ የሆኑ አዳዲስ አባላት ተመርጠው ከታች እስከ ላይ ያሉ ያመራር ቦታዎችን <u>እንዲይዙና</u> ድርጅቱን የወቅቱ ፈታኝ ሁኔታ በሚጠይቀው መሰረት <u>እንደገና</u> ከውስጥና ከውጭ በሁሉም እረድፍና ዕርከን አጠናክረው በአንድ አሃዳዊ ማዕከላዊ አመራር በአገር ውስጥና በውጭ አገር እንዲያደራጅ አባላትን እንዲያበራክቱ፣ በዓላማና በትግል ፅናት እንዲያንፅና ትግሉን አስፋፍተው አርቅቀው እንዲታገሉ፣ ድልን ለሕዝብ እንዲያስጨብጡ ከአደራና መሃላ ጋር መምረጥ ነው።

ስለዚህ የመኢአድ ሐቀኛ አባላት፣ ደጋፊዎችና አገር ወዳድ የሆናችሁ ሁሉ ፓርቲው በአሁኑ ወቅት ወደ አደገኛ የመፍረስ ሁኔታ የደረሰውን የአመራር ችግር፣ ድክመት፣ ቅሌትና የፖለቲካ ብቃት ማነስ በመገንዘብ መኢአድ ነኝ ያለውን ያፈነገጠ ሁሉ ከመርዳት ተቆጥበን በሐቅ በእውነትና በዓይነት ሕጋዊ መኢአድና ኢትዮጵያዊነት ያለውን ባሕሪ የያዘ ቆራጥ የኢትዮጵያ ልጆች እንዲታገሉ የሚያደርግ ጠንክሮ እስከሚወጣ፤ ከላይ ያቀረብነው አሳብ በፍጥነት ሥራ ላይ እንዲውል አጣዳፊ ድጋፋችሁና ትብብራችሁን በመጠየቅ፣ ትግሉ የሚጠይቀው ለአገርና ለሕዝብ ጥቅም ጥርት ያለ አቋምና ፅናት፣ በመስዋዕትነት ላይ መስዋዕትነትን ለመክፈል ዝግጅነትን፣ ለአገር ከሃቀኞችና የፖለቲካ ፅናት ካላቸው ጋር መቆም ስለሆነ ይህን የኢትዮጵያ <u>አድን</u> ብሔራዊ ጥሪ እናቀርባለን።

ትብብራችሁና ድጋፋችሁ ከጐደለና የወያኔ ስላዮች በድርጅቱ ውስጥ ሰርገው መሰናክል ሆኑ ከላይ የወያኔ የውስጥ መረጃ እንዳመለከተው ሁኔታዎች ወደ ሌላ አቅጣጫ ተሸጋግረው አገርና ሕዝብ የበለጠ የሚጎዱ መሆናቸውን በቅድሚያ እናሳስባለን።

*በመኢአድ አዲስ አመራር*

*የኢትዮጵያ ድል ይረጋገጥ!!!*